# የአቶ መኮንን ደጀኔ ወልደሰንበት አጭር የህይወት ታሪክ



1941 - 2012

አቶ መኮንን ደጀኔ ወልደሰንበት (መኩሪያ) ከአባቱ ከአቶ ደጀኔ ወልደሰንበት እና ከናቱ ከወ/ሮ ብዙነሺ ሀብተወልድ በቀድሞው የሸዋ ክፍለ ሀገር በዬረርና ከረዪ አውራጃ ናዝሬት ከተማ በ1949 ዓ.ም ተወለደ ። አቶ መኮንን እድሜው ለትምህርት ሲደርስ የአንደኛ ትምህርቱን በዚያው በናዝሬት እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በአጼ ገላውዲዮስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከአጠናቀቀ በኋላ ባህርዳር በሚገኘው የፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ገብቶ የሚሰጠውን ሥልጠናና ትምህርት አጠናቋል። ከዚያም በሲዳሞ ክፍል ሀገር በመምህርነት ተመድቦ ለበርካታ አመታት በአንደኛና በሁለተና ድረጃ ትምህርት ቤት በማስተማር ላይ እያለ በ1966 ዓ.ም በኢትዮጵያ የተከሰተው ለውጥ ሲመጣ መኩሪያም እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወጣት ለለውጡ መምጣት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ሲያደርግ ስለነበር የመጣውን ለውጥ በጸጋ ተቀብሎ ትግሉን ቀጠለ። ከዚያም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ሲመሰረት መኩሪያም ግንባር ቀደም በመሆን ወደ ኢህአፓ ከተቀላቀሉ ምሁራን አንዱ ነበር።

በሲዳሞ ክፍለሀገር  እና በአካባቢው ባሉ አውራጃዎችና ትንንሽ ከተማዎች የኢህአፓን መዋቅር በህቡዕ በመዘርጋት፤ የድርጅቶን ፕሮግራም በማስተዋወቅና መምህራንን በመመልመል ከፍተኛ አስተዋጸዖ ያደረገ ትጉህ ታጋይ እንደነበር በአካባቢው አብረውት የድርጅት ሥራ ከሰሩና ከእራሱ አንደበት የተረጋገጠ ነው።

በከተማው አካባቢ የሚደረገው የህቡዕ ድርጅታዊ ሥራ በወታደራዊው ደርግ የጸጥታ እመቃ ምክንያት አስጊ በሆነበት ጊዜ ቀደም ብለው

በህብረተሰቡ የተጠረጠሩትን እንደ መኩሪያ አይነት ታዋቂ ሰዎችን በአካባቢው የመኖር ተስፋ የሚያሰጋ ስለነበር በድርጅቶ መሰመር በህቡዕ በመጓዝ ትግራይ ክፍለ ሀገር አጋሜ አውራጃ ውስጥ ወደ ሚገኘው የኢ.ህአፓ ሰራዊት (ኢ.ሕአሠ) በ1968 ዓ.ም ተቀላቀለ።

በኢ.ህአፓ ሰራዊት (ኢ.ሕአሠ) ወስጥ የሚሰጠውን ወታደራዊ ስልጠና ወስዶ እንደ ጨረሰ መደበኛውን ኃይል ተቀላቅሎ ትግሉን ቀጠለ።

አቶ መኮንን ደጀኔ ወልደሰንበት በጣም ንቁ እና ቆራጥ ታጋይ በመኑ ከተራ ተጋዳይነት በአጭር ጊዜ ውስጥ የኃይል ኮሚሳር በመሆን ታጋይና አታጋይ ሆነ። ከዚያም የሰራዊቱ አንድ ክንፍ በውሎ አድርጎ ወደ ጎንደር ሲሻገር መኮንንም በነዚያ ኃይለታት ውስጥ ነበር። ወደ ጎደር ጠለምት ከተሻገረ በኋላም የሰራዊቱ የኃይል ኮሚሳር ሐላፊነቱን እንደያዘ በመቀጠል በብቃትና በቆራጥነት በጠለምት፤ በበዬዳና በበለሳ ለበርካታ ዓመታት በትጋት መርቷል።

በበለሳና አካባቢው በተደረጉ ጦርነቶች የተሰጠውን ግዳጅና ሀላፊነት በብቃት በመወጣቱ በበለሳ የሚንቀሳቀሰው የሰራዊት ቀጠና (ሪጅን 3) አመራር ሆኖ ተመደበ። በአዲሱ ምድብ ቦታው ለአመታት በብቃት ኃላፊነቱን ሲወጣ ከቆዩ በኋላ በበለሳ በሚገኘው ሰራዊት ውስጥ በተፈጠረው ችግር ምክንያት ጠለምት ከሚገኜው ሰራዊት ጋር ተቀላቅሎ ለትንሽ ጊዜ ከተነቀሳቀሰ በኋል ሰራዊቱን ለቆ ወደ ሱዳን ገባ።

በሱዳን ለጥቂት ጊዜ ከቆዬ በኋላ የአሜሪካ መንግሥት በሰጠው የሰፈራ ፕሮግራም እድል ሰላገኘ ወደ አሜሪካ መጣ። በመጀመሪያ በአትላንታ ጆርጃ ለጥቂት አመታት ከቆዬ በኋላ ወደ ካሊፎርኒያ በመምጣት

መጀመሪያ በኦሬንጅ ካውንቲ ከዚያም ወደ ሎስ አንጀለስ በመዛወር ኑሮውን ጀመረ።

አቶ መኮንን ደጀኔ ወልደሰንበት አሜሪካ ከመጣ በኋላም በወጣትነቱ የጀመረውን ትግል በመቀጠል በውጭ የሚገኘውን የኢህአፓን መዋቅር ተቀላቅሎ ከሪጅን አመራርነት እስከ ከፍተኛ የድርቱ አመራርነት እስከ ህይወቱ እልፈት ድረስ የድርጅቱ አባል ሆኖ ቀጥሏል

አቶ መኮንን (መኩሪያ) እጅግ አገር ወዳድ፤ ከራሱ ይልቅ የአገሩን ጉዳይ የሚያስቀድም ብሩህ ኢትዮጵያዊ መሆኑን አብረውት በትግል ዓለም የኖሩ ሁሉ የሚመሰክሩት ሐቅ ነው። አቶ መኮንን ከእምነቱ ፍንክች የማይል ፤ ለጓዶችና ልድርጅቱ ታማኝ፤ ግዴታውን የሚያውቅ ትጉህ ታጋይ ነበር።

አቶ መኮንን ከወይዘሮ ፈለቀች በቀለ ጋር ትዳር መሥርቶ ይኖር ነበር።

አቶ መኮንን በአደረበት ድንገተኛ ህመም ምክንያት ለጥቂት ጊዜ በሆስፒታል ሲረዳ ከቆዬ በኋላ መጋቢት 6 ቀን 2012 ዓ.ም በተወለደ በ71 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

አቶ መኮንን በቅርብ ወዳጅ ዘመዶቹ ተውዳጅ፤ ትግባቢና በጣም የተከበረ ስው ነበር።

ነብሱን በአጸደ ገነት ያኑርልን

ባለቤቱ ወ/ሮ ፈለቀች በቀለና

ጓደኞቹ

# ከትግል ጓዱ

እኔ ጓድ መኩሪያ የማውቀው አሲምባ ከ1968 በኢትዮጵያ አቆጣጠር ማለቂው: ወይም 1969 መጀመርያ ጀምሮ ሲሆን የጓድ መኩርያን ማንነት በደንብ ያውኩት ግን ቀጠና 3 ወይም በለሳ በሚባለው ቀጠና ሁለታችንም የቀጠናው አመራር ኮሚቴውስጥ በምንሰ ራበት ጌዜ ነው::

ጓድ መኩርያ በጣም በሳል ሁለገብ አመለካከት ያለው( በፖለቲካውም በወታደራዊለማ ለት ነው) ነገሮችን በሁሉም አቅጣጫ የሚያይና ተጨባጭ ሁኔታወችን
አስቀድሞ በማየት ውሳኔዎችን ለመወሰን ከፍተኛ አስተዋፆ የሚያደርግ በጣም
እጅግ ትሁት ጓድ ነበር::

ጓድ መኩርያ በኮሚቴ ለመሥራት በጣም ምቹና የተሰጠውን የሥራ ክፍፍል በሙሉልብ የሚቀበል; የተቀበለውንም ሀላፊት በአግባቡ በተውሰነው ጌዚያቶች በስዓቱየሚያቀርብ ጠንካራ ጓድ ነበር::

ከጓድ መኩርያጋር በሥራ በአሳለፍኳቸው ጌዚያት ውስጥ በኩሚቴ ሥራ የሚያምን; በ ስብሰባወች ጌዜ የሚያምንበት ሁሉ ለኮሚቴው አባላት በአግባቡ በማቅረ
በሀሳቡ ተቀባይነት እንድያገኝ ከፍተኛ ጥረት የሚያደርግ ሀሳቡ ከወደቀ ግን የተወሰነ ውን ውሳኔ በሙሉ ልብ ተግባራዊ የሚያደርግ ቅን ጓድ ነበር::

ጓድ መኩርያ ለጓዶቹ ያለው ፍቅር እጅግ በጣም ከፍተኛ ሩሁሩህ ነበር ይህንንምፍቅሩን በተለያዮ ሁኔታዎች ተግባራዊ የሚያደርግ ውድ ጓድ ነበር::

ውድ የከፉ ቀን ጓደ; ጓድ መኩርያ በል እንግድህ እግዚአብሔር ነፍስህን በገነትያኑራት እ ያልኩ እሰናበትህ አለሁ

የአሲምባውና የበለሳው ጓድህ

ደበበ እጅጉ

አትላንታ ጆርጅያ::




ከረዥም ጊዜ ጓደኞቹና ጓዶቹ ጋር



ከጋሻ ማህበር አባሎች ጋር